# ሁሉም ሰው በሕግ ፊት እኩል ነው

ኢብሳ ነመራ

አምነስቲ ኢንተርናሽናል  ኢትዮጵያ ውስጥ የሰብአዊ መብት ጥሰት ይፈፀማል የሚል ድርሰት ከሚያዘጋጁ ዓለም አቀፍ ተቋማት አንዱ ነው፡፡ ኢትዮጵያ ላይ የዚህ አይነት ድርሰት መድረስ አይሰለቸውም፡፡

የማይሰለቸው ከጀርባ ሆነው አገራት ሊመሩበት ይገባል የሚሉትን የኢኮኖሚ ፖሊሲ ሊያሰፉላቸው የሚፈልጉ ወገኖች ስላሉ ነው፡፡ ይህን ያለልክ የተሰፋ ፖሊሲ እስኪቀበሉ በሃሰተኛ ክስ ሊያሳጡዋቸው ቆርጠው ተነስተዋል፡፡ ለዚሁ አላማ ማስፈፀሚያም በጀት ይመድባሉ፡፡

በሰብአዊ መብት መለዮ ስር ተሸሽገው የዚህ አይነት ዓላማ ለማስፈፀም የገንዘብ ልገሳ ከሚቀበሉት መሃከል አንዱ አምነስቲ ኢንተርናሽናል ነው፡ ፡ይህን ካላደረጉ ልገሳው ይቆማል፡፡ ልገሳው ከቆመ ሕልውናቸው ያከትማል፡፡ እናም ለጋሾቻቸው ያዝ ያሉዋቸውን መንግስታት ሳይሰለቹ መጨበጫ የሌለው "የሰብዘዊ መብት ጥሰት ይፈፅማሉ" በሚል ውንጀላ ሳይሰለቹ ያጥላላሉ፡፡

ኢትዮጵያ ውስጥ የሰብአዊ መብት ጥሰት ይፈፀማል እያሉ በተደጋጋሚ ሲያወጡዋቸው የቆዩት ሃሰተኛ ክሶችና ውንጀላዎች ሪፖርቱ የወጣበትን ግዜ ካላየን በስተቀር አንዱ ከሌላው የማይለይ ቢሆንም፣ አሁንም "መሰረተ ቢስ ወሬ እያወራችሁ ነው" ብሎ መልስ መስጠት ተገቢ ይመስለኛል፡፡ አምነስቲ ኢንተርናሽናል በቅርቡ "50ኛ ዓመታዊ ሪፖርት" በሚል ኢትዮጵያን በሚመለከት ያወጣው ሪፖርት ላይ የግሌን ምላሽ መስጠት አስፈላጊ ሆኖ አግኝቼያለሁ፡፡

አምነስቲ ኢንተርናሽናል "50ኛ አመታዊ ሪፖርት" በሚል በቅርቡ ይፋ ባደረገው ሰነድ "የኢትዮጵያን መንግስት በተመለከተ ተቃዋሚዎችን እያፈነና ጋዜጠኞችን እያሳደደ ሰብአዊ መብቶችን ከማክበር ይልቅ የኢኮኖሚ ዕድገት ላይ አተኩሯል" ማለቱን  አንብበናል፡፡

የአምነስቲ ኢንተርናሽናል የአፍሪካ ዳይሬክተር የሆኑት ኤርዊን ቫንደር ቦርት ድርጅታቸው ካወጣው ሪፖርት ጋር አያይዘው ለአሜሪካ ድምፅ ሬድዮ በሰጡት ማብራሪያ፣ "ኢትዮጵያ ባለፉት ሰባት ዓመታት 11 በመቶ የኢኮኖሚ እድገት በማስመዝገብ 83 ሚሊየን ሕዝቧን ከድህነት ለማውጣት እየሞከረች ነው፡፡ ይሁንና የፖለቲካ ቂጥጥሩ ካልላላ የአኮኖሚ እድገት የትም እንደማያደርስ ከሰሜን አፍሪካ አገራት መማር ይቻላል" ሲሉ ገልፀዋል፡፡

ዳይሬክተሩ ኢትዮጵያ ውስጥ አሳሳቢ ያሉትን ጉዳዮች አንስተው፣ የሲቪክ ማህበራትና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን አዋጅ፣ የተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲዎች አባላትና የጋዜጠኞችን መታሰር ጠቅሰዋል፡፡ ቀደም ሲል እንደገለፁኩት እነዚህ የአምነስቲ ኢንተርናሽናል ክሶች አዲስ አይደሉም፡፡ ከዚህ ቀደም በተደጋጋሚ የሰማናቸው የተለመዱና የሰለቹ ወሬዎች ናቸው፡፡

አምነስቲ ኢንተርናሽናል በሪፖርቱ እና በኃላፊዎቹ መግለጫ ኢትዮጵያ ሕዝቧን ከድህነት ለማውጣት የኢኮኖሚ ዕድገት ማስመዝገቧን አምኗል፡፡ ይህ በራሱ ለልማቱ መፋጠን የሰብአዊ መብት መከበር ለመኖሩ አንዱ ማረጋገጫ መሆኑን እፅንኦት ሊሰጠው ይገባ ነበር፡፡ ሰብአዊ መብቱ የተጣሰበት ህብረተሰብ እንዴት ሆኖ የመንግሥትን ፖሊሲ አምኖ በመቀበል ሊተገብር፤ ለልማት ሊነሳሳና ተጨባጭ ውጤት ሊያመጣ በዚህም ተጠቃሚነቱን ሊያረጋግጥ እንደሚችል ለማሰብ ሳይንሳዊ ወይም ምክንያታዊ ትንታኔ ማቅረብ በእውነቱ አስቸጋሪ ነው፡፡ እነ ሂዩማን ራይትስ ዎች በየጊዜው በሚያወጧቸው ሪፖርቶቻቸው ላይም ይህን እውነታ ለመግለጽ ፈጽሞ አይፈልጉም፡፡ በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ እኮ የልማቱ ባለቤትና አንቀሳቃሽ ሞተር ሕዝቡ ራሱ መሆኑን አምኖ መቀበል ግድ ይላል፡፡ የልማት ፖሊሲውም የዜጎችን ሁለንተናዊ ተጠቃሚነትና የልማት ባለቤትነትን በሚያረጋግጥ መልኩ ተፈጻሚ ለማድረግ ተዘጋጅቶ የወጣ መሆኑን ልብ ማለት ያስፈልጋል፡፡

የኢኮኖሚ ዕድገት በተጨባጭ ለሰው ልጅ ህይወት መሰረታዊ ፍላጎቶች የሚያሟሉ ምርቶች መመረታቸውን፣ አገልግሎቶች መሰጠታቸውን ያመለክታል፡፡ ይህ መሆኑ ደግሞ የመብቶች ሁሉ ምንጭ የሆነውን መሰረታዊው በሕይወት የመኖር መብት መሟላቱንና መሟላቱ ዋስትና ማግኘቱን ያመለክታል፡፡ የኢኮኖሚ እድገት ለዜና ፍጆታነት ውሎ የሚያበቃ ግንጥል ጌጥ ሳይሆን የሰብአዊ መብቶች መከበርን ማረጋገጫ ዋና መሳሪያ መሆኑ ሊሰመርበት ይገባል፡፡

የአምነስቲ ኢንተርናሽናል ኃላፊዎች ግን የኢኮኖሚ እድገቱ ከሰብአዊ መብት መከበር ጋር ያለውን ዝምድና፣ መንግስት በኢኮኖሚ ዕድገት ሕዝቡን ከድህነት (በሕይወት ለመኖር ከሚያስፈልጉት ነገሮች እጦት) ለማላቀቅ የሚያደርገውን ጥረትና ለሰብአዊ መብት መከበር ያለውን ቁርጠኝነት እንደሚያሳይ አድርገው ማቅረብ አልመረጡም፡፡ ስኬቱ በገንዘብ ድጋፍ ሕልውናቸውን የሚያስጠብቁላቸውን ምእራባውያን ቡድኖችና ግለሰቦችን ስለማያስደስት ነው ይህን ማድረግ ያልፈቀዱት፡፡

ከዚህ ይልቅ ፈጥረው ያቀረቡት “የሰበአዊ መብት ጥሰት ይፈፀማል” የሚል መሰረተ ቢስ ውንጀላ ላይ ተንጠልጥለው “የኢኮኖሚ እድገታችሁ በሰሜን አፍሪካ አገራት ከተቀሰቀሰው አመፅ አያስጥላችሁም” ብለው ሊያስፈራሩ ነው የሞከሩት፡፡

እርግጥ ነው በሰሜን አፍሪካ አገራት፣ ቱኒዚያ፣ ግብፅና ሊቢያ በሕዝባዊ አመፅ የመንግስት ለውጥ ተካሂዷል፡፡ በእነዚህ ሀገራት ባለፉት አመታት የኢኮኖሚ እድገት መመዝገቡም ዕውነት ነው፡፡ የለየለት አምባገነን የነበረውን የሊቢያውን የጋዳፊ መንግስት እንተወውና በቱኒዚያና በግብፅ የነበረውን ሁኔታ - በተለይ ከኢኮኖሚ ዕድገት ጋር በተያየዘ ያለውን ገፅታ በግርድፉ እንመልከት፡፡

በቱኒዚያና የግብፅ ኢኮኖሚ የድኅማ ኢኮኖሚ ነበር፡፡ በእነዚህ አገሮች ሲመዘገብ የነበረው የኢኮኖሚ ዕድገት ሁሉንም ዜጋ በሀብት ፈጠራ በማሳተፍ የተገኘ ሳይሆን፣ በተወሰኑ ሴክተሮች በጥቂቶች ተሳትፎ የተመዘገበ ነው፡፡ የተቀረው ሕዝብ ከዚህ የኢኮኖሚ ዕድገት ተጠቃሚ የሚሆነው በተለያየ መንገድ በሚደረግ ድጎማ ነበር፡፡

በግብፅና ቱኒዚያ መጨረሻ ላይ የነበረው ሁኔታ መጠናኛ ልዩነት ሊኖረው ቢችልም፣ ዓለም ከገጠማት የኢኮኖሚ ቀውስ ጋር ተያይዞ በተለይ በግብፅ “ሕዝቡ ካሁን በኋላ ምንም ሊያመጣ አይችልም” በሚል የተሳሳተ  ስሌት ድጎማው ቀደም ሲል በነበረበት እንዳይቀጥል የተደረገበት ሁኔታ ነበር፡፡  ይህ ሁኔታ በተለይ በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚኖረውን ሕዝብ አስከፍቶት ነበር፡፡ ይህም ከሌሎች የሰብአዊ መብት ጥሰቶች ጋር ተዳምሮ በቀላሉ ለአመፅ እንዲነሳሳ የሚደርገው ስነልቦናዊ ሁኔታ እንዲፈጠር አድርጓል፡፡

የኢትዮጵያ መንግስት በተቃራኒው የድጎማ ፖሊሲን አይከተልም፡፡  ልማታዊ ፖሊሲን የሚከተል መንግስት ነው፡፡  ሕዝቡን ማኖር፣ ኑሮውን ማሻሻል የሚፈልገው በተወሰነ ሴክተር የሚፈጠር ሃብት በድጎማ ወደታች በማንጠባጠብ አይደለም፡፡ ከዚህ ይልቅ ትኩረት ያደረገው አብዛኛው ሕዝብ የራሱ የሆነ ሃብት እንዲፈጥር ማስቻል ላይ ነው፡፡ በተለይ ያለፉ ስምንት አመታት የኢኮኖሚ ዕድገት የተመዘገበው አብዛኛው ሕዝብ የራሱን ሀብት መፍጠሩ በመቻሉ ነው፡፡

የኢትዮጵያ መንግስት 80 በመቶ የሚሆነውን የአገሪቱን ሕዝብ የሚወክለውና በአነስተኛ ማሳ ላይ በእርሻ ስራ የሚተዳደረውን አርሶ አደር ምርታማነትን ለማሳደግ ልዩና ቀዳሚ ትኩረት ሰጥቷል፡፡ ለእያንዳንዱ አርሶ አደር ማሳው ድረስ በመሄድ ምርታማነቱን የሚያሳድግ የሙያ ድጋፍ እንዲያገኝ አድርጓል፡፡ የተሻሉ የምርት ግብአቶች ምርጥ ዘርና ማዳበሪያ አቅርቧል፡፡ የተሻሉ የምርት ግብአቶችን የመግዛት አቅም እንዲኖረው የገንዘብ ብድር አገልግሎት አመቻችቷል፡፡ እነዚህ ሁሉ ተዳምረው የአርሶ አደሩን ምርታማነት በማሳደግ ቀደም ሲል ያልነበረውን ሀብት መፍጠር አስችለዋል፡፡ ባለፉት ስምንት አመታት በተመዘገበው የኢኮኖሚ እድገት ውስጥ የግብርናው ዘርፍ የላቀ ድርሻ ነበረው፡፡

በከተማ ያለውን ሁኔታ ስንመለከት መንግስት ለስራ አጦች የእለት ጉሮሯቸውን የሚደፍኑበት ድጎማ የመስጠትን አካሄድ አልመረጠም፡፡ በግልና በማህበር ተደራጅተው በሚችሉትና አዋጭ ሆኖ ባገኙት

የማምረትና አገልግሎት የመስጠት ሥራ ላይ ተሰማርተው ራሳቸውን እንዲችሉ የብድር አገልግሎት የመስጠትን አካሄድ ነው የመረጠው፡፡

አብዛኞቹን የከተማ ስራ አጦች ከስራ ውጭ አድርጎ እጃቸውን ያሰራቸው የገንዘብ እጦት በመሆኑ በዚህ ሁኔታ በመላው የአገሪቱ ከተሞች በጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት የታቀፉ በመቶ ሺህ የሚቆጠሩ ሥራ አጦች የራሳቸውን ስራ በመስራት ሀብት ፈጠራ ውስጥ ገብተዋል፡፡

በከተሞች አካባቢ በተመዘገበው የኢኮኖሚ እድገት ውስጥ ከፍተኛውን ድርሻ የያዘው የኮንስትራክሽን ዘርፍም ለበርካታ ዜጎች የስራ እድል በመፍጠር በኢኮኖሚ ዕድገቱ ውስጥ በመሳተፍ ራሳቸውን ችለው የሚኖሩበትን እድል ፈጥሯል፡፡

በአጠቃላይ የኢትዮጵያ የኢኮኖሚ ዕድገት ሕዝቡ ራሱ በሀብት ፈጠራ ላይ እንዲሰማራ የማድረግ ልማታዊ አቅጣጫን የተከተለ ነው፡፡ በመሆኑም ህዝቡን በመንግስት ላይ እንዲያምፅ የሚያነሳሳ ኢኮኖሚያዊ ነባራዊ ሁኔታ በአገሪቱ ውስጥ የለም፡፡ ውጭ አገር ባሉ፣ አገርም ውስጥ በሚንቀሳቀሱ አንዳንድ ተቃዋሚዎች የአረቡን ዓለም እንቅስቃሴ ተከትሎ ህዝቡ ለአመፅ እንዲነሳሳ ያደረጉት ጉትጎታ ምላሽ ያጣው በዚህ ምክንያት ነው፡፡

እርግጥ አሁንም በሃብት ክፍፍል ረገድ ክፍተቶች ይታያሉ፡፡ የዚህ ክፍተት ዋነኛ መንስኤ ዜጎች በተለይ ከፍተኛ ገቢ ያላቸው ዜጎች በሕጉ መሰረት መክፈል የሚገባቸውን ያህል ግብር አለመክፈላቸው ነው፡፡ በዚህ ረገድ በተለይ ካለፈው አመት ጀምሮ የተሻለ ስራ እየተሰራ ነው፡፡ አሁንም ግን ብዙ ይቀራል፡፡

እንግዲህ አምነስቲ ኢንተርናሽናል "የኢኮኖሚ እድገታችሁ ከሰሜን አፍሪካው አይነት አመፅ አያስጥላችሁም" በሚል ያቀረበውን ተጨባጭነት የሌለው ምኞት አዘል ሃሳብ ትክክለኛ ለማስመሰል "መንግስት የተቃዋሚ ፓርቲ አመራሮችንና ጋዜጠኞችን አስሯል" የሚል መደገፊያ  አቅርቧል፡፡

እርግጥ ነው   ስራቸው ጋዜጠኝነት የሆነ አንድ ሁለት ሰዎች በቁጥጥር ስር ውለው ክስ እንደተመሰረተባቸው፣ ከእነዚህ መሃከል የቅጣት ውሳኔ የተላለፈባቸው እንዳሉ መገናኛ ብዙሃን ነግረውናል፡፡ ፖለቲከኞች ነን የሚሉ ሰዎችም እንዲሁ መታሰራቸውን ሰምተናል፡፡ ዋናው ጉዳይ የእነዚህ ሰዎች በቁጥጥር ስር መዋል ሳይሆን "በምን ምክንያት በቁጥጥር ስር ዋሉ ?" የሚለው ነው፡፡

የኢትዮጵያ ሕገመንግስት ማንኛውም ዜጋ የፈቀደውን አመለካከት የመያዝ፣ የመግለፅ በግሉና ከመሰሎቹ ጋር ተደራጅቶ አመለካከቱን የማራመድ፣ ለፖለቲካ ስልጣን የመወዳደር መብት ሰጥቷል፡፡ ማንኛውም ዜጋ ሃሳቡን በነፃነት የመግለፅ መብቱም ተረጋግጧል፡፡ ይህን ሃሳብን የመግለፅ መብትን በአግባቡ ለመተግበር ይረዳ ዘንድ የመገናኛ ብዙሃንና የመረጃ ነፃነት ሕግ ወጥቷል፡፡

በዚሁ መሰረት አንዳንዶቹ "በአገሪቱ የፖለቲካ ፓርቲዎች በብዛት መደራጀታቸው አላስፈላጊ ነው" በሚል ትችት እስኪያቀርቡ ድረስ፣ በርካታ የፖለቲካ ፓርቲዎች ተደራጅተው ህጋዊ ዕውቅና አግኝተው በመንቀሳቀሰ ላይ ናቸው። አንድም የእነዚህ ፓርቲዎች አባል ወይም አመራር በያዘው አቋም ምክንያት ተጠይቆ አያውቅም፡፡ በርካታ የግል ጋዜጦችና የኤፍ ኤም ሬዲዮ ጣቢያዎች ተቋቁመው በተለይ አንዳንድ ጋዜጦች የሙያ ስነምግባርና የሚጥሱ ሃሳቦችን እስከማሰራጨት በዘለቀ ሁኔታ በስራ ላይ ይገኛሉ ።

ፖለቲከኛ ወይም ጋዜጠኛ መሆን ግን በግልፅ ወንጀል ተብለው የተደነገጉ ድርጊቶችን የመፈፀም፣ የማስፈፀምና የመደገፍ መብት አያሰጥም፡፡ በመሆኑም ወንጀል ፈፅመው የተገኙ የፖለቲካ ፓርቲ አባላትና ስራቸው ጋዜጠኝነት የሆኑ ግለሰቦች እንደማንኛውም ተጠርጣሪ ወይም ጥፋተኛ ግለሰብ በፍርድ ቤት ትዕዛዝ በቁጥጥር ሰር ውለው በሕግ አግባብ ክስ ይመሰረትባቸዋል፡፡ በዚሁ መሰረት በይፋ ችሎት በተከሰሱበት ጉዳይ እየተከራከሩ የፍርድ ሂደታቸውን በመከታተል ላይ የሚገኙና የቅጣት ውሳኔ የተላለፈባቸውም አሉ።

"ጋዜጠኞች ይታሰራሉ" የሚለውን የአምነስቲ ኢንተርናሽናል ውንጀላ በተመለከተ በመገናኛ ብዙሀን በይፋ የተገለፁ መረጃዎች እንደሚያሳዩት፣ አንድም በጋዜጠኝነት ስራው ባስተላለፈው ዘገባ፣ ወይም ባስተላለፈው ሃሳብ የታሰረ የለም፡፡ ስራቸው ጋዜጠኝነት የሆኑ በህግ የተደነገገን የወንጀል ድርጊት በመፈፀም ወንጀል ተጠርጥረው በቁጥጥር ስር የዋሉ፣ ጥፋተኛነታቸው በማስረጃ ተረጋግጦ የቅጣት ውሳኔ የተላለፈባቸው ግለሰቦች ግን አሉ።

ሰዎች ጋዜጠኛ በመሆናቸው ብቻ ከመሃንዲስ፣ ከሃኪም፣ ከመምህር ... የተለየ ወንጀልን መፈፀም የሚያስችል ከለላ የላቸውም፡፡ አምነስቲ ኢንተርናሽናል "ጋዜጠኛ ወንጀል ቢሰራም አትንኩ" እያለን ነው። በሌላ አነጋገር "ጋዜጠኞች የሌሎችን ሰበአዊ መብት የመጣስ መብት ይኑራቸው" እያለ መሆኑ ሊስተዋል ይገባል፡፡ አምነስቲ ኢንተርናሽናልን ገንዘብ እያጎረሱ የሚያስለፈልፉት ቡድኖችና ግለሰቦች በሚኖሩበት አገር ጋዜጠኞች ወንጀል የመፈፀም ፍቃድ ይኖራቸው ይሆን እንዴ?

የፖለቲከኞችን መታሰር በተመለከተ ወንጀል ፈፅመዋል በሚል ተጠርጥረውና በቁጥጥር ስር ውለው ክስ የተመሰረተባቸው፣ የተቃዋሚ ፓርቲ አባላት ሊኖሩ ይችላሉ፡፡ በቁጥጥር ስር ውለው የተከሰሱና ቅጣት የተወሰነባቸው የተቀዋሚ ፓርቲ አባላት ነን የሚሉ ግለሰቦች ብቻ ሳይሆኑ፣ የገዢውን ፓርቲ አባላትም ጭምር መሆናቸውን ልብ በሉ። ወንጀል ፈፅመዋል የተባሉ በርካታ የገዢው ፓርቲ አባላት በቁጥጥር ስር ውለው የፍርድ ሂደታቸውን እየተከታተሉ ይገኛሉ፣ የተፈረደባቸውም አሉ።

ታዲያማ አምነስቲ ኢንተርናሽናል “ጋዜጠኞችና ፖለቲከኞች ወንጀል ቢፈፅሙም መነካት የለባቸውም” እያለ “ሁሉም ሰው በሕግ ፊት እኩል ነው” የሚለውን መሰረታዊ የፍትህ መርህ እየተፃረረ መሆኑን ልብ በሉ፡፡